የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ		
I. አጠቃላይ መግለጫ		
የመስሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ባዮሜዲካል ኢንጂነር II	ባዮሜዲካል
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XII	
መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት		
II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት		

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡

- የመካከለኛና ከፍተኛ ህክምና መሳሪያዎችን አስፈላጊነት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ፤ ፤ተከላ በማከናወንና በማማከር፤ እንዲሁም በመሳሪያዎች አጠቃቀም ዙርያ ለጤና ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት የጤና አገልግሎቱን ሥራ መደገፍ ነው።

2.2.ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፡ የህክምና እቃዎችን ፍላጎት ዳሰሳ በማድረግ ስፔስፊኬሽን ማዘጋጀት እና የህክምና መሳሪያዎች ተከላ ማከናወን፣

- የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት መረጃዎች ያሰባስባል/ቅጾችን ያዛጃል/መረጃውን ይተነትናል/ፍላጎት በመለየት ይዘረዝራል፣
- የህክምና መሳሪያዎች ወቅታዊ ዋጋ ያሰላል(stock value estimation)/ዋጋቸው የወረዱ የሕክምና መሳሪያዎች እንዲተኩ (replacement) ለአፈጻጸም ያቀርባል
- በህክምና መሳሪዎች ግዢ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፣ የጨረታ ቴክኒካል ግምገማ መረጃ በማደራጀት ተሳትፎ ያደርጋል
- የሚገዛዉን መሳሪያ በመለየት ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፣ መረጃ ያጠናቅራል

- የመካከለኛ በህክምና መሳሪዎች መለዋወጫ የሚዉሉ መሳሪያዎች እንዲገዙለት ያደርጋል
- አዲስ ለሚገቡ ከፍተኛ ህክምና መሳሪያዎች በስፔስፊኬሽን መሰረትና በተጠቃሚው ፍላጎት መግባቱን ይመረምራል/ተሟልተው መቅረባቸውን ያረጋግጣል፣
- በአምራች የተሰጡ የተከላ ማንዎሎችን በመከተል የመካከለኛ የህክምና መሳሪያዎች ተከላ ቦታ መረጣ ያከናዉናል/ተከላውን ይከታተላል
- አቅራቢው ድርጅት የመጀመሪያ ጊዜ ስልጠና በከፍተኛ ህክምና መሳሪያዎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ጥገና ዙርያ ለተጠቃሚውና ለባዮሜዲካል ባለሙያ ስሰጥ ተሳትፎ ያደርጋል
- ከህክምና መሳሪያ አቅራቢ ጋር ያሉ ስምምነቶችን ያስተዳድራል።
- በክምችት ክፈል ያሉ ከፍተኛ ህክምና መሳሪያዎች ዝርዝር መያዝና በፍላጎት ዳሰሳ መሰረት የስርጭት ድልድል ይሰራል

ውጤት **2**፡ የመካከለኛ እንዲሁም የከፍተኛ የህክምና መሳሪያዎችን አያያዝ፤አግባባዊ አጠቃቀምን ማስፈንና አገልግሎት ልሰጡ የማይችሉትን ማስወገድ።

- የመካከለኛና ከፍተኛ የህክምና መሳርያዎች አግባባዊ አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል።
- የመካከለኛና ከፍተኛ የህክምና መሳርያዎች ተጠቃሚዎችን ዕለታዊ የቅድመ ብልሽት ክብከቤ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል።
- በመካከለኛ ከፍተኛ የህክምና መሳርያዎች ዙሪያ ሥልጠና ይሰጣል።
- የመካከለኛና ከፍተኛ የህክምና መሳርያዎች በወጣው ፕሮግራም መሰረት ወርሃዊ የቅድመ ብልሽት ክብከቤ ያደርጋል።
- የመካከለኛና ከፍተኛ የህክምና መሳርያ ፐርፎርማንስ ቼክ እና ማስተካከያ (adjust) ያደርጋል።
- ባዮሜዲካል ስራ አመራር መመሪያዎችና ፖሊሲዎች ይተገብራል።
- በእርዳታ የሚሰጡ መሳሪያዎችን በአገር አቀፍ ህግ መሰረት ተሟልተው መቅረባቸውን አረጋግጦ ይረከባል
- በሆስፒታሉ አገልግሎት ጊዜያቸዉን የጨረሱና ደግመዉ በመታደስ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት የከፍተኛ የህክምና መሳሪያዎችን በመለየት እንዲወገዱ ለአስወጋጅ ኮሚቴ ያቀርባል።
- የመካከለኛና ከፍተኛ የህክምና መሳሪያዎችን አግባባዊ አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል
- አዳዲስ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ማስተዋወቅ

ውጤት **3** ፤ የህክምና መሳርያዎችን መፈተሸ፤መጠገን፤ ማደስ

- የጥገና ትዕዛዛትን በመቀበል የብልሽት ምክንያትና ደረጃ መለየት፣የተበላሹ አካላትን ጥገና ያደርጋል
- ህክምና መሳሪያዎች መለዋወጫ ይለውጣል
- ለጥገና የሚያገለግሉ መለዋወጫዎች ግዥ ጥያቄ ያቀርባል
- በመካከለኛ የህክምና መሳርያዎች ጥገና መረጃ ይይዛል

ውጤት **4** የህክምና መሳሪያዎችን አገልግሎት የማስተዳደር ተግባራትን ያከናውናል።

- የህክምና መሳሪያዎችን እና መለዋወጫዎች ቆጠራና ምዝገባ ያከናዉናል፣ መረጃውን በዳታቤዝ አደራጅቶ ይይዛል/ሪፖርት ያደርጋል/ወቅቱን ጠብቆ አፕዴት ያደርጋል
- የህክምና መሳሪያዎች በተመለከተ መረጃ ጥራት ያረጋግጣል/ይቆጣጠራል
- ባዮሜዲካል ስራ አመራር መመሪያዎችና ፖሊሲዎች ዝግጅት ላይ ሀሳብ በማቅረብ ይሳተፋል/ፖሊሲዎችን ይተገብራል/አተገባበራቸውን ይገመግማል/ የማሻሻያ ሀሳቦችንም ያቀርባል
- የጥገና ስራዎችን ጥያቄዎችንና ትዕዛዛትን ይቀበላል/ ይመራል/አፈጻጸማቻቸውን ይገመግማል
- የታካሚዎችና የጤና ባለሞያዎች የስራ አከባቢ ደህንነት ያረጋግጣል
- የህክምና መሳሪያዎች አመታዊ ምርመራ(ድያጋኖስስ) ያካሂዳል/ ትክክኛነታቸውን ያረጋግጣል(calibration and verification)

- የህክምና መሳሪያዎች ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ
- የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች የስጋት ዳሰሳ(risk assement) ያካሂዳል፣ ይተነትናል፣ የስጋት ምንጮችን በመለየት የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል

III. የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

3.1 የሥራ ውስብስብነት

- ሥራው የህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናትን ማካሄድን፤ ግዥን ማመከርንና ቴክኒካል ስፔስፍኬሽን ማዘጋጀትን፤ በርዳታ የሚሰጡና አዳዲስ የሚገዙ መሳሪያዎችን መመርመንን፤ የተከላ ቦታ ማመቻቸትና ተከላውን ማከናወን፣ ለመለዋወጫ የሚዉሉ መሳሪያዎች እንዲገዙ ማድረግ፣ የቅድመ ጥገና ፕሮግራም ማዘጋጀት እና ተገቢውን የጥገና እና ካሊብሬሽን ሥራ ማከናወን፤ መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ከዋሉ በሁዋላ መከታተልን፤ የአገልግሎት ግዚያቸው ሲያልቅ ማስወገድን ማከናወን ሲሆን በስራ ሂደትም ምቹ የተከላ ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ መሆን፣ ሥለመሳሪያዎች አተካከልና አጠጋገን የሚያስረዳዉ ማንዋል አለመቅረብ፣ ስለመሳሪያ ተከላና አጠጋገን ከአምራቹ ወይም ከአቅራቢው ድርጅት በቂ ስልጠና አለማግኘት እና የመለዋወጫ እቃዎች የአቅርቦት ችግር መከሰት የሚያጋጥም ሲሆን የተለያዩ አማራጮችን ወስዶ የመሳርያ መትከያ ቦታዎችን በማዘጋጀት፣ ስለመሳርያው አጠቃላይ ሁኔታ የሚያስረዱ ማንዋሎች እንዲቀርቡ በማድረግ፣ ከመሳሪያ አቅራቢው ድረጅት ሥልጠና በመውሰድ እና የመለዋወጫ እቃዎች የሚገኙበትን አማራጭ በማየትና ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ መፍታትን፣ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥገናዎችን ዕውቀት ና አመዛዛኝነት በመጠቅም መፍታትን ይጠይቃል።

3.2 ራስን ችሎ መስራት

3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ***ሥራው የመሳሪያዎች የአጠቃቀም ደንብና በመመሪያ ከቅርብ ሃላፊ በሚሰጥ አጠቃላይ መመሪያ በአሰራር መመሪያዎች እንዲሁም የአሰራር መርሀዎችን መሰረት በማድረግ የሚከናወን ነው።።***

3.2.2 ***ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ***

- ***ሥራው የጥገናና ተከለ ሥራው የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ስለማከናወኑ በመጨረሻ በኃላፊው ግምገማ ይደረግበታል።።***

3.3. ተጠያቂነት

3.3.1. ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት፣

- የህክምና መሳሪያዎች ግዢ ሲካሄድ ሙያዊ ምክር ባይሰጥ፣ ቴክኒካል ስፔስፊኬሽን ባያዘጋጅ፤ የተከላ ቦታ ባያመቻችና ተከለውን ባያከናውን፣ ለመለዋወጫ የሚዉሉ መሳሪያዎች በወቅቱ እንዲገዙ ባያደርግ፣ የቅድመ ጥገና ፕሮግራም ባያዘጋጅና ተገቢውን የጥገና እና ካሊብራሽን ሥራ ባያከናውን እንዲሁም መሰረታዊ የኤሌክትሪክ ደህንነት ቁጥጥር ባያድርግ፤መወገድ ያለባቸውን መሳሪያዎች በአግባቡ ባያስወግድ፤ ደረጃቸውን ያልጠበቁ መሳሪያዎች እንዲገዙ ያደርጋል፤ መሳሪያው የሚጠበቅበትን ያክል ጊዜና አገልግሎት እንዳይሰጥ ያድረጋል፣ በድርጅቱ የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ያስተጓጉላል፣ በድርጅቱ የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ያስተጓጉላል፣ በመሳርያው

ተጠቃሚ የጤና ባለሙያና በህሙማኑ ላይ መስተጓጎል ይፈጥራል።

3.3.2. ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- **የለበትም**

3.4 ፈጠራ

- ሥራው የጤና አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችን ተከላ ማከናወንና ሲበላሹም ጥገና ማድረግ እንዲሁም ማስወገድ ሲሆን የመሳሪያዎች አጠቃላይ ሁኔታ የሚያስረዳ ማንዋል ባልተገኘበት ወቅት እና በጥገና ወቅት የመለዋወጫ እጥረት ቢገጥም የመሳርያውን ባህሪ ተረድቶ ስራውን ማከናወን እና መጠነኛና ከፍተኛ የሞዲፊኬሽን ስራዎችን በመስራት ስራውን ውጤታማ ማድረግን ይጠይቃል።

3.5. የሥራ ግንኙነት

3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- **ሥራው ከቅርብ ሃላፊው፣ከባልደረቦቹ፤ ከተገልጋዮች እንዲሁም ከመሳሪያው ሻጭ ድርጅት ጋር የሥራ ግንኙነት ማድረግን የጠየቃል።።**

3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- **የሥራ መመሪያን ለመቀበል፣ለማማከር ፤ ስለ ስራው መረጃና ድጋፍ ለመስጠት፤ ሥራን በጋራ ለመስራትና ድጋፍ ለማግኘት፣ እንዲሁም ከመሳሪያው አቅራቢ ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ለመወያየት የሚደረግ ነው።።**

3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ከስራ ጊዜው እስከ 50 በመቶ ይሆናል

3.6 ኃላፊነት

3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- **የለበትም ።።**

3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- **የለበትም ።።**

3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ

- **የለበትም ።።**

3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት

- ሥራው ለተከላ፤ለጥገና እንዲሁም ለካሊብሬሽን የሚያገለግሉ የ ዎርክሾፕ መሳሪያዎችን እና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች (computer, laptop, printer....) መያዝና መጠቀም አለበት። ግምቱም እስከ ብር 5,000,000.00 ብር ይሆናል።

3.7. ጥረት

3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- የህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናትን የማካሄድን፤ ግዥን ሲፈፀም የማማከርንና ቴክኒካል ስፔስፍኬሽን የማዘጋጀት፤ በርዳታ የሚሰጡና አዳዲስ የሚገዙ መሳሪያዎችን የመመርመ፤ የተከላ ቦታ የማመቻቸትና ተከላውን የማከናወን፣ ለመለዋወጫ የሚዉሉ መሳሪያዎች እንዲገዙ የማድረግ፣ የቅድመ ጥገና ፕሮግራም የማዘጋጀት እና ተገቢውን የጥገና እና ካሊብሬሽን ሥራ የመስራት ፤ መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ እያሉ የመከታተል፤ የአገልግሎት ግዚያቸው ሲያልቅ መርሆችን ጠብቆ የማስወገድን የአዕምሮ ውጥረት የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከስራ ጊዜው እስከ 60 በመቶ ይሆናል።

3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት

- **ሥራው በተደጋጋሚ ከቅርብ ሀላፊው፤ከባልደረቦቹ፤ከመሳሪያው ተገልጋዮቹ እንዲሁም ከመሳሪያው አቅራቢ ጋር በሚያደርጋቸው ግኙኝነቶች የሚነሱ የተለያዩ አለመግባባቶችን(ትችት፤ማጥላላት፤ወዘተ) ተቃቁሞ ስራውን ውጤታማ ለማድረግ የስነ ልቦና ዝግጁነትና ቁርጠኝነት እንዲኖረው ይጠይቃል።**

3.7.3 የዕይታ ጥረት፣

- **ስራው ከኢንተርኔት የመሳሪያዎችን አተካከልና አጠጋገን የሚያስረዳ ማንዋልና መረጃዎችን መፈለግን እና ጨረር አመንጭ የሆኑ የህክምና መሳሪያዎችን መትክልና መጠገን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም የአይታ ጥረትን ይጠይቃል ይህም ከስራ ጊዜው እስከ** 50 **በመቶ ይወስዳል።**

3.7.4 የአካል ጥረት

- **ሥራው** 30% **በመቀመጥ፤** 30% **በመቆም፣**20% **በመንቀሳቀስ፣** 20 **በመቶ በመንጋለል የሚከናወን ነው።**

3.8. የሥራ ሁኔታ

3.8.1. ሥጋትና አደጋ

- በሥራው ወቅት በጋሉ የመሳሪያ ክፍሎች አማካኝነት ለቃጠሎ፣ የህክምና መሳሪያዎች አማካኝነት የመቆረጥና በከፊል የሰውነት ክፍልን ማጣት እንዲሁም በአግባቡ ባልተዘረጉ የመብራት መስመሮች ለሚከሰት የኤሌክትሪክ ንዝረት ይጋለጣል።

3.8.2. የሥራ አካባቢ ሁኔታ

- ሥራው ጎጂ ለሆኑ በሽታ አምጭ ተዋስህያንን፤ ጨረርና መርዛማ ኬሚካሎች ባሉነት የሚከናወን ሲሆን ይህም በቆዳ በአይን እንዲሁም የመሃንነት ችግር በማስከተል ለከፍተኛ ለጤና መታወክ ሊያጋልጡ ይችላሉ።

3.9. እውቀትና ክህሎት፣

3.9.1. ትምህርት

የትምህርት ደረጃ	የትምህርት አይነት
መጀመሪያ ድግሪ	**ባዮሜዲካል ኢንጅነሪንግ**

3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ	ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት
3 ዓመት	**በባዮሜዲካል ኢንጅነሪንግ**

የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም	ፊርማ	ቀን

የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	ፊርማ	ቀን